## ተስፋ የቆረጠ መንግስት ተንኮል ከመስራት አይቆጠብም

የወያኔ ኢህአዲግ መንግስት የፖለቲካ ሥልጣን ከጨበጠ 15 አመት ሆኖታል። በነዚህ 15 አመታት ውስጥ ግን አንድም ጊዜ የህዝቦችን ድጋፍና አመኔታ አላገኘም። እስከ አሁን በስልጣን ላይ ሊቆይ የቻለው በህዝቦች ፍቃደኝነት ሳይሆን ከፋፍለህ ግዛ በሚለው በአምባገነኖችና ጸረ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች መመሪያ በመጠቀም ድርጅቶችን በድርጅቶች ላይበማነሳሳት፣ ለዘመናት በሰላም አብረው የኖሩትን ህዝቦች በማዋጋትና በማጋጨት ነው። ይህንን እኩይ ተግባሩን በመገንዘብ ትግላቸውን በማቃናጀት የስርአቱን ዕድሜ ለማሳጠር 5 ተቃዋሚ ድርጅቶች ከቅርብ ጊዜ በፊት የነፃነትና የዲሞክራሲ ህብረት መፍጠራቸው ይታወሳል። ወያኔ ይሆናል ብሎ ያላሰበው ይህ ህብረት መፈጠሩ እንቅልፍ ነስቶት አዲስ የተፈጠረውን የተቃዋሚዎች ህብረት አፈርሰዋለሁ በሚል ተንኮል ተቃዋሚ ድርጅቶችን የሚያራርቅና  የሚያጋጭ እንድሁም ህዝቦች በመተማመን የጋራ ችግሮቻቸውን በጋራ እንዳይፈቱ ለማድረግ እየተንቀሳቀሰ ነው።

ወያኔ ኦነግና ቅንጅት አብሮ መሥራት አይችሉም።
ተቃዋሚ ድርጅቶች ተቀራርበው ትግላቸውን በማቀናጀት አብረው መሥራት እስካልቻሉድረስ ደግሞ ኢህአዲግን የሚያሰጋው የለም በማለት በየመድረኩ ሲናገር እንደነበር ይታወሳል። ይሁን እንጂ ተቃዋሚ ድርጅቶች በወያኔ ኢህአዲግ እውን ሊሆን አይችልም የተባለውን ህብረት በመፍጠር የወያኔን ጎራ አደናገጡት። እነዚህ የነፃነትና ዲሞክራሲ ህብረት የፈጠሩ ድርጅቶች ሀገሪቷን ለዘመናት ሰላም የነሳትን ችግር ለመፍታት መስማማታቸው ደግሞ ወያኔን ይበልጥ ቀኑ እንዲጨልምበት አድርጎታል። በመሆኑም ይህ ጸረ ህዝብ ቡድን የተፈጠረውን ህብረት ቢቻለው ለማፍረስ ካልተቻለው ደግሞ ሊያደናቅፈው ዘርፈ ብዙ የሀሰት ፕሮፖጋንዳ መንዛት ጀምሯል።

ይህ የወያኔ ኢህአዲግ የሀሰት ፕሮፖጋንዳ ህብረት በመሰረቱ ድርጅቶችመካከል ጥርጣሬ እንዲነግስ በማድረግ ላይ ያነጣጠረ ነው። ለዚህም ወያኔ ኢህአዲግ ራሱ ያዘጋጀውን ጹሑፍ በኦነግ ስም በማሰራጨት ላይ ይገኛል። ኢትዮጵያ በ2009 ይህን ትመስላለች በሚል ካርታ በመቅረጽ ህዝብን ከህዝብ ሊያዋጋ እየጣረ ነው። ይሁን እንጂ የወያኔ ተንኮልና ተግባር ለሚገነዘቡ ኃይሎች ሁሉ ይህ አዲስ አይደለም፣ አሳሳቢም አይሆንም።

ወያኔ ኢህአዲግ ከአሁን በፊት ኦነግን በኦሮሞ ህዝብ እንዲጠላ ለማድረግ የሀሰት ፊልም በማንሳት ለህዝብ ሲያሳይ እንደነበረ ይታወቃል። በበደኖ ዜጎችን ፈጅቶ የኦነግ ስራ ነው በማለት ተቀባይነትን ለማግኘትያደረገው ጥረት ከትዝብት ላይ ጣለው እንጂ ላሰበው አላማ ስኬታማነት እገዛ አላደረገለትም። በጅማ፣ ሲጊሞና ጋቲራ በባሌ እንዲሁም በሌሎች አካባቢዎች ህዝባችንን አርዶ ፊልም በማንሳት የኦነግ ተግባር ነውሊያስብል ያደረገው ጥረትም ሰሚ ጆሮ አላስገኘለትም። ይበልጥ ህዝቡ
የወያኔን ቡድን ደባ በመገንዘብ ይህ ቡድን ስልጣን ላይ ለማቆየት  ኢ ሰብአዊ ድርጊቶችን ከመፈጸም ወደ ኋላ የማይል መሆኑን አረጋገጠ። ከዚህም በተጨማሪ እነዚህን አረመኔያዊ ድርጅቶች በህዝባችን ላይ
ሲፈጽሙ የነበሩት የወያኔ ኢህአዲግ አባላት መሆናቸው በድርጊቱ ላይ ተሳታፊ የነበሩ የስርአቱ ታማኞች ያጋለጡት ጉዳይ ነው።

በአሁኑ ወቅትም የስርአቱ ቁንጮ መለስ ዜናዊ "ትብብር በመፍጠር
ላይ የኦነግ የትኩረት አቅጣጫ" በሚል ርዕስ ስር የጻፈውን ጽሑፍ ከኦነግ የተገኘ ሚስጥራዊ ሰነድ ብሎ በማሰራጨት ላይ ይገኛል። ።
የዚህ ጽሑፍ አለማ ኦነግን፣ ቅንጅትንና ሌሎችንም የህብረቱን አባላት በማቃቃር ላይ ያለመ እንደሆነ ግልጽ ነው። ይህ የወያኔው ጠቅላም ሚኒስትር አጸያፊ ድርጊት ጊዜውን ጠብቆ እንደሚጋለጥ አንጠራጠርም።

በሀገር ውስጥ የታፈነውን የህዝቦች ድምጽ ውጭ ሀገሮች ያሉት ዜጎች ከፍ አድርገው ማሰማታቸው ስላስደነገጠው ይህንን እንቅስቃሴ ለመከታተልና ለመቆጣጠር በሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ በማፍሰስ የዲያስፓራን ጉዳይ የሚከተል አዲስ መዋቅር በሚኒስቴር ደረጃ አዋቅሮ እንቅስቃሴ መጀመሩ ወያኔ ምን ያህል እንደተደናገጠ ያሳያል። በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ተቃዋሚ ድርጅቶች ከተናጥል ትግል በህብረት መታገልን ምርጫቸው አድርገው የነፃነትና የዲሚክራሲ ህብረት መመስረታቸው የተቋቋመው የዲያስፓራ ሚኒስቴር እንደማይሰራ ከማረጋገጡም በሻገር የወያኔን ቡድን ይበልጥ ብርግጎ

የሚይዘውንና የሚተውውን አሳጥቶቷል።

በመሆኑም የነፃነትና የዲሞክራሲ ህብረት ሳይጠናከር ማፍረስ አለብን በማለት እየተንቀሳቀሰ ነው። ይህንንም እኩይ አላማ ለማሳካት በሀገር ውስጥ ህዝቡን ከህዝብ በማጋጨትና ውዥንብር በመንዛት ለማወናበድ እየሞከረ ነው። በገጠሩ ህዝቦችን ለማዋጋት በትምህርት ቤቶች ተማሪዎችንበብሄር ከፋፍሎ ለማጋጨት ሸር እየሸረበ ይገኛል። ህዝቦችን ማጋጨትና ሰላም መንሳት ደግሞ በህዝቦች የተጠላና ተስፋ የቆረጠ መንግስት የሚፈጽመው ተግባር ነው።

በመሆኑም በሀገር ውስጥ የምትገኙ እንዲሁም በስደት አለም በተለያዩ ሀገሮች ውስጥ የሚትገኙ ሁሉ ወያኔ እየሸረበ ባለው ተንኮል ሳትዘናጉ አጥብቃችሁ እንድትከላከሉት መልዕክታችንን እያስተላለፍለን። የኦሮሞ ህዝብም እንደ ከአሁን በፊቱ በወያኔ ተንኮል ላይ በመንቃት ተስፋ ከመቁረጥ በመነጨ የሚሸርበው ሴራ ግቡን እንዳይመታ ከሌሎች ህዝቦች ጋር እጅ ለእጅ በመያያዝ ትግሉን እንድታፋፍም በድጋሚ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን። የወያኔ ኢህአዲግም ሆነ የተለያዩ ጸረ ህዝብ ቡድኖች ለሚነዙት የሀሰት ፕሮፖጋንዳ ጆሮ አትስጥ። እየተጓዝን ያለነው በሀቅ ጎዳና አላማችንም ግልጽ በመሆኑ እንደምናሸንፍ አንጠራጠርም።

**ድል ለኦሮሞ ህዝብ**
**የኦሮሞ ነፃነት ግንባር**
**ሰኔ** 8 **ቀን** 2006